# የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግሥት
# የትራንስፖርት መምሪያ

**አንቀጽ 6፣ አድልዎ አልባ ፖሊሲ**

በ1964 የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እና ተመሳሳይ ድንንጋጌዎችን (በ 23 CFR 200.9 አፈፃፀም) መሠረት በማድረግ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በብሄር፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ ወይም በአካለ ስንኩልነት ምክንያት DDOT ከፌደራል ከሚያገኛቸው ወይም ካገኛቸው የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች እንዳይካፈል መከልከል ወይም አድልዎ እንዳይደስበት ማረጋገጥ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የትራንስፖርት መምሪያ (DDOT) ፖሊሲው ነው። በተለይም በአድልዎነት እንዳይፈፀሙ ከሚከለከሉት መካከል፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፡ አንድን ግለሰብ ማንኛውንም አገልግሎት፣ የገንዘብ እርዳታ ወይም ፕሮግራሙ ከሚያቀርበው፣ ተጠቃሚ ሊያደርገው ወይም ሊያደርጋት ከሚያስችላቸው ጥቅማ ጥቅም፤ በመጠን፣ በጥራት ወይም የአገልግሎቱን ወይም የጥቅማ ጥቅሙን የልማድ አካሄድ ላይ ልዩነት ማድረግ፣ ወይም በማንኛውም ጉዳይ ላይ አገልግሎትን በመቀበል፣ እርዳታ ወይም ጥቅማ ጥቅምን በዘር፣ በቀለም፣ በብሄር፣ በፆታ፣ በዕድሜ ወይም በአካለ ስንኩልነት ላይ ተመስርቶ ግለሰቦችን የየብቻ ምደባ ወይም በተናጠል ማስተናገድን የሚከለክል ነው።

ሕጉ በከፍተኛ ስፋት እስከፈቀደ ድረስ፣ የሰውን ልጅ ጤንነት እና የአካባቢ ሁኔታን የሚያውኩ ነገሮችን በመለየት እና አናሳ እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ሕዝቦች ላይ ባልተመጣጠነ ሁኔታ ከፍተኛ እና ጥላቻን ያዘለ ተፅእኖን ለማስወገድ፣ በአስተዳድር፣ ፕሮግራሞቹ እና በፖሊሲዎቹ ላይ DDOT ቅንነቱን ያረጋግጣል። በተጨማሪም፣ DDOT የተወሰነ የእንግሊዘኛ ችሎታ ላላቸው ሰዎች ተገቢውን ስሜት በሚሰጥ ሁኔታ አገልግሎቶቹን እንዲያገኙ ያበረታታል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ DDOT በፕሮግራሞቹ የፌደራል የገንዘብ እርዳታ አገኙም አላገኙም በሁሉም ፕሮግራሞቹ እና እንቅስቃሴዎቹ፣ አድልዎ እንዳይፈጸም ለማድረግ፣ ማንኛውንም ጥረት እንደሚወስድ ያረጋግጣል። በተጨማሪም፣ DDOT የፌደራል እርዳታ ገንዘብን ወደሌላ አካል በሚያሰራጭበት ወቅት፣ በአንቀጽ 6 የተደነገገ ደንቦች በሁሉም ስምምነቶች ላይ ያካትቶ እና ለድንጋጌው ተገዢነታቸውን ይከታተላል።

የአንቀጽ 6 ተገዢነት የፌደራል የገንዘብ እርዳታዎችን ለመቀበል መስማማት ነው። የአንቀጽ 6 አስተናባሪ Taneshia Dublin የዚህ ፖሊሲ እና ሕግ አተገባበር ላይ፤ 23 CFR 200.9 እና 49 CFR 21 የሚያስገድደውን ወይም የሚከተላቸው ድንጋጌዎችን ጨምሮ፣ ተገዢ መሆንን ለማስፈፀም እና ለማረጋገጥ ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰቷቸው ተወክለዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የDDOT ተባባሪ አስተዳዳሪዎች በፕሮግራሞቻቸው ዙሪያ አንቀጽ 6/አድልዎ አልባ ፕሮግራም ድንጋጌዎችን ለማስፈፀም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰቷቸው ተወክለዋል።

Sharon Kershbaum
ዳይሬክተር፣ የዲስትሪክቱ የትራንስፖርት መምሪያ

9/27/2024
ቀን